የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ ሀምሌ ፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 35
ADDIS ABABA 14th July, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፭/፳፻፲፫

ላልተማከለ ኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ..........................ገጽ ፲፫ሺ፬፻፷፬

## Content

Proclamation No1255/2021

International Development Association Loan Agreement for Financing Access to Distributed Electricity and Lighting Ethiopia Project Ratification Proclamation..……………...Page 13464

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፭ /፳፻፲፫**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ላልተማከለ ኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሶስት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፫፻፵፯ ሚሊዮን ፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሚያዚያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ባካሄደው ፭ኛ ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO.1255/2021**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Three Hundred Forty-Seven Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 347,100,000.00) for financing Access to Distributed Electricity and Lighting Ethiopia Project, was signed in Addis Ababa on 23rd day of April, 2021;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 5th special session held on 7th day of July, 2021;

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ላልተማከለ ኤሌክትሪክና መብራት አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፉ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፶፭/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሚያዚያ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6857-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሶስት መቶ አርባ ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር. (፫፻፵፯ ሚሊዮን ፩፻ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopian Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing Access to Distributed Electricity and Lighting Ethiopia Project Ratification Proclamation No. 1255/2021".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 6857-ET signed in Addis Ababa on 23rd day of April, 2021 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Three Hundred Forty-Seven Million One Hundred Thousand Special Drawing Rights (SDR 347,100,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 14th Day of July, 2021**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**